# "ትግል ወሬ



በዛሬው ዕትማችን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ሊቀ መንበር የሆኑትን በአዲስ አበባ ካዛንችስ ተወልደው ያደጉትንና ለአለፉት 15 ዓመታት በሰሜን አሜሪካ ነዋሪ አቶ ነሲቡ ስብሐትን ይዘንላችሁ ቀርበናል። በሙያቸው ጂኦፊዚስት የሆኑትንና "ፍፁም ነው እምነቴ የከፍተኛ 15 (ካዛንችስ እና አካባቢው) ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ" ደራሲ፣ የ"ያ ትውልድ ተቋም" መስራች እኝህ ሰው የሕይወት ታሪክና ያሳለፉበትን ፖለቲካዊና ማዕበራዊ ሕይወት የዳሰሰ ቃለ መጠይቅ ወደፊት ለማቅረብ ቃል እየገባን በዚህ አምዳችን ስለ ድርጅታቸው ዓላማና እያከናወኑ ስላለው እንቅስቃሴ ያስረዱን ዘንድ ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ ይዘንላችሁ ቀርበናል። መልካም ንባብ።

ጠያቂ ፦ አቶ ነሲቡ ስብሐት ድርጅታችሁ "አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መች ተመሠረተ? ዓላማውስ ምንድን ነው?

አቶ ነሲቡ ስብሐት፦ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ፖለቲካዊ ድርጅት ነው። ድርጅቱ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. (September 18, 2016) ፕሮግራሙን፣ ማንፌስቶና www.ethiopiachen.org ድረ ገጽ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በሰሜን አሜሪካ ተመሠረተ።

"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ከተመሠረተ ጀምሮ በሀገር ቤትና በውጭው ዓለም ለፍትህና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል አስፈላጊውን አስተዋጽዖ እያደረግን እንገኛለን። የማንነታችን መግለጫና የዓላማችንና የአቋማችን ማንጸባረቂያ የሆነው ልሳናችን "ኢትዮጵያችን" በሀገራችን ወቅታዊ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ቅኝት፣ ትችት፣ ትምህርት ይዛ ቢያንስ በወር አንዴ ትወጣለች። በተጨማሪም በሀገሪቱ ድንገተኛ ክስተት በሚፈጠርበት ወቅት፣ የሀገራችንን ታሪካዊ ክብረ በዓላት ለማስጠበቅ "ኢትዮጵያችን" ልዩ ዕትም ትወጣለች።

ስለ ኢትዮጵያችን ይህን ያህል ካልኩ የኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ ዓላማዎች ዝርዝር በፕሮግራማችንና ማንፌስቷችን በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን ይህንንም በድረ ገፃችን www.ethiopiachen.org ማግኘት ይቻላል። ጠቅለል አድርጎ ለማስቀመጥ የድርጅታችን ዋና ዋና ትኩረቶችና "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄና" ፖለቲካ ድርጅት ሊመሠረት ያስፈለገበት ዋና ዋና ዓላማ፦

- በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ ከማንም ሳንደራደር "አንድ ኢትዮጵያ" ብለን በመነሳታችን

- ኢትዮጵያ የሁሉም ዘሮች፣ ጎሳዎች/ነገዶች ሀገር መሆኗን ተቀብለን ሁሉንም በእኩልነት የምትመለከት "አንድ ሕዝብ" ብለን መነሳታችን

- የግለሰብና የዜግነት መብትን ቀዳሚ ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን እውን እንዲሆን

- የሕዝብን ፍላጎት የሚያካትትና ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ላይ ትኩረት የሰጠ ለትውልድ ዘለቄታ ያለው ሕገ መንግሥት ለማርቀቅና ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለንን አስተዋጽዖ ለማድረግ

- ወጣቶችና ሴቶችን ያሳተፈ ጠንካራ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ ለመመስረት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ

- ኢሕአዴግ/ህወሓት ለ27 ዓመት የተከሉትን የዘርና/ቋንቋ ከፋፍለህ ግዛ አካሄድ እንዲያበቃና ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ያብብ ዘንድ ለተወሰነ ዓመታት ሀገሪቷ በጋራ አመራር ትጓዝ ዘንድ በቀረበው በማንፌስቶአችን ሠነድ መሠረት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የጋራ ኅብረት ስምምነት ይፈጠር ዘንድ አስተዋጽዖ ለማድረግ

- በተለይ በአለፉት አርባ ዓመታት የትግል ታሪክ የአገዛዝ ሥልጣናቸውን ተገን አድርገው የሀገር ሀብትና ንብረት የዘረፉ፣ የሕዝብ ልጆችን ሕይወት የቀጠፉ ወንጀለኞች ጉዳይ ሕግ እንዲመለከተውና በቀጣይነትም በሚደረገው ብሔራዊ ዕርቅ በሀገርና ሕዝብ ላይ የደረሰውን በደል እውቅና ሰጥቶ መጓዝ የሚቻልበትን አቅጣጫ ለመቀየስ

- በመጨረሻም በአሁኑ ወቅት ብቅ ያለው የለውጥ ሂደት መሠረታዊ የሀገሪቷን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ችግሮች ይፈታ ዘንድ ትግሉን በሀገር ቤት አጠንክሮና ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ ተማሪዎችን ይበልጥ ትኩረት ሰጥቶ መስራት

በማስፈለጉ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"ና የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋሙን አምነንበታል።

# አይደለም።

## አቶ ነሲቡ ስብሃት

ጠያቂ ፦ በአሁኑ ጊዜ እንደሌሎቹ ድርጅቶች በሀገር ቤት እየተንቀሳቀሳችሁ ነው ወይ?

አቶ ነሲቡ ስብሐት፦ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ነሐሴ 21 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ በሀገር ቤት የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ነው። ንቅናቄው ትግሉን ሙሉ በሙሉ ሀገር ቤት በማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሚጠሩ ስብሰባዎችም ሆነ በምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ አማካይነት በተደረጉ ስብሰባዎች እየተሳተፍን እንገኛለን። የእኛ ዓላማ መንግሥት በሚጠራቸው ስብሰባዎች እየተገኙ በተሌቪዥ᎐ን መስኮት መታየት ብቻ አይደለም።

ለእኛ ለኢትዮጵያችን ትግል ዓላማ ነው። ትግል የማያቋርጥ ጉዞ ነው። በመሆኑም ስንጀምረው ቃል የገባነውን ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለሕዝባችን አንድነት የምናደርገው ትግል እንደ ጅምራችን ዛሬም፣ ነገም፣ ከድል በኋላም ይቀጥላል። በመሆኑም አሁን የተገኘውን ሀገር ቤት በመጠኑም ቢሆን የተከፈተውን የመንቀሳቀስ ዕድል ተጠቅመን የማደራጀትና ፕሮግራማችንን፣ ዓላማችንን እያስተዋወቅን መሥራት ነው የምንፈልገው። ለዚህም ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ የማሰባሰብ ሥራ እያከናወን እንገኛለን። የሚዲያዎች አድሎነት እንደተጠበቀ በአገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያችን ንቅናቄ ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ ለሕዝባችን ለማስተዋወቅ እንጥራለን። የድርጅታችን ልሳንም “ኢትዮጵያችን” ቀደም ሲል በወር አንዴ እናወጣ ነበር አሁን እንደውም በ15 ቀን አንዴ ለንባብ እንዲበቃ እናደርጋለን።

በውጭው ዓለምም (ሰሜን አሜሪካን ጨምሮ) በሁሉም አህጉራት አሁን ደግሞ በሀገራችን ድርጅታዊ ጥንካሬአችንን ለማጎልበት አባላትንና ደጋፊዎችን እያሰባሰብን ነው። ግልጽ እንዲሆን ግና የምንፈልገው በኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ በተለይ በአባልነት የምናካትተው ጊዜያቸውን ሰውተው የሚሠሩትን ነው። ትግል ባዶ ጩኸት አይደለም። ትግል ወሬ አይደለም። ትግል ዓላማ ነው። ትግል ከገንዘብ ይበልጥ ጊዜ መስጠትን ይጠይቃል። ትግል ዕውቀትን ይሻል። ትግል ችሎታን ይሻል። ትግል ብቃት ያለው አመራርን ይፈልጋል። በጥቅሉ ትግል ሕይወትን ጨምሮ በርካታ ማንነታችንን ይጠይቃልና በዚህ መልኩ ነው የእኛ ስብስብ። አዎ ለእንቅስቃሴአችን ገንዘብ፣ ቁሳቁስ ሌላም ዕርዳታ ያስፈልገናል። ይህንንም ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ በኩል የሚረዱንንም ወገኖች እንፈልጋለን፣ እናሰባስባለን።

ጠያቂ፦ አቶ ነሲቡ ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ጠቅሰዋል ይህን ቢያብራሩልን?

አቶ ነሲቡ ስብሐት፦ የኢትዮጵያን አንድነት አስጠብቀን ሕዝባዊ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኙ ዘንድ ይዘን በተነሳነው ዓላማ ትግሉን ከግብ ለማድረስና “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር” የምንለው ዋናው መፈክራችን ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ትኩረታችንን በአሁኑ ወጣት ትውልድ ላይ አድርገናል። ወደድንም ጠላንም የነገይቱ ኢትዮጵያ የነሱ ናትና። ከእኛ ከአንጋፋዎቹ የትግል ታሪክ ጠንካራውንም ደካማውንም ጐን ገምግመውና ትምህርት ቀስመውበት አሁን ከአለው የዓለምና የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ትግሉን ቀጥለው ለድል በማብቃት ኢትዮጵያንና ሕዝባችንን ከተደቀነባቸው መከራና ሥቃይ ያላቅቁ ዘንድ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው።

ግልጽ ለማድረግም ይበልጥ የትግሉ አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆኑ የምንፈልገው የዛሬውን ትውልድ አካላትን ነው። ቀጣይ ሀገሪቷ የነሱ ናትና። የኢሕአዴግን/ወያኔን ማንነትና ምንነት አብረው እየኖሩ፣ መከራውን እየተጋሩ፣ እስሩን እየታሰሩ፣ ድብደባውን እየቻሉ፣ ሞትን እየተጋፈጡ ያሉትን አደራጅተን ስንታገል የነገውንም ዕድል እናሰፋለንና ትኩረታችን በሀገር ቤት በዚህ መልኩ ነው። እርግጥ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ጉዞ ነው።

ኢሕአዴግ በ27 ዓመት አገዛዙ ወጣቶችንና ታዳጊ ሕፃናትን ከልጅነታቸው ጀምሮ በዘር ፖለቲካ እየሰበከ ነው ያሳደጋቸው። በተጨማሪ ኢትዮጵያ ሀገር አፍቃሪ፣ ሰንደቅ ዓላማውን አክባሪ፣ ለሕዝብ ተሚጋች ተተኪ ትውልድ እንዳይኖራት እጅጉን ዘምቶባቸዋል። ብቁና ተተኪ ትውልድ የሌላት ሀገር እንደተሸመደመደች ትኖራለችና የኢሕአዴግ/ህወሓት የ27 ዓመት ትውልድ ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ ባይሳካም ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊነቱን ከነሰንደቅ ዓላማው ከፍ ያደረገ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የጀግኖች አባቶቹን/እናቶቹን ታሪክ ደጋሚ ዜጋ ይሆኑ ዘንድ እንጥራለን።

ወጣቶች ባዕድ አምላኪ በመሆን ሀገራቸውን እንዲዘነጉ፣ በተለያዩ ሱሶች እንዲጠመዱ ለምሳሌ መጠጥ፣ ጫት፣ ሲጃራ፣ በሺሻ፣ ከዚህም አልፎ በአሸሽ የመሳሰሉት ውስጥ ተጠምደው እንዳይማሩ፣ ብቁ ዜጋ እንዳይሆኑ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ ኢሕአዴግ/ህወሓት እንደ አንድ ፕሮጀክት ሰርቶባቸዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ተሸርሽሮ ስለ ሀገራቸው ሳይሆን ስለ ዘራቸው ብቻ እንዲያስቡ፣ ከራሳቸው ዘር/ጎሳ/ነገድ ሌላ ስለሌላው እንዳያገባቸው ይሆን ዘንድ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ አእምሯቸው ይህን ይቀበል ዘንድ በአካባቢ፣ በትምህርት ቤት ከፍተኛ ዘመቻ በመንግሥት ደረጃ ተጥሯል። የሚያደርጉትን የዕለት ተለት እንቅስቃሴ ለመከታተል “አንድ ለአምስት” በሚል የስለላ መረብ ወጥመድ ውስጥ ተሰቃይተዋል። ለአለፉት 50 ዓመታት ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ቀዳሚ ሁነው የታሰሩት፣ የተሰቃዩት፣ የተገረፉት፣ የተገደሉት ወጣቶች በኢሕአዴግ ዘመንም ትውልድ ይህን መከራ ሲቀበሉ ነው የኖሩት። ከፖለቲካው እርቀው እንዲቀመጡ የመጣ መንግሥት ሁሉ በተለይ ደርግ በቀይ ሽብር ጭምር ያሽመደመደውን ትውልድ ተንተርሶ ኢሕአዴግም አሰቃይቷቸዋል። ከዚህ ጋር በተጨማሪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ሳይቀሩ ወጣቱን መጠቀሚያ እያደረጉት አስከፊ ጊዜ ሲመጣ አውላላ ሜዳ ላይ ሲጥሉት ተስተውሏል።

ቢዘረዘር በማያልቀው በዚህ ሁሉ መከራ ያደጉት ሕፃናት የዛሬ በሰላሳዎቹ መጨረሻ ላይና ከዚያ በታች ያሉትን ወጣቶች ስሜታቸውንና ጉዳታቸውን ተረድቶ የሚንከባከባቸው እንደገና አይዟችሁ የሚላቸው፣ የሚያበረታታቸው፣ ስቃዩ፣ መከራው በሀገርና በሕዝብ የመጣ ነው ለዚህ ደግሞ በፍርሃት መከበብ ሳይሆን ቆርጦ መታገል መሆኑን ከጎናቸው ሁነን እየሠራን እነኚህ ወጣቶች በራሳቸው ዕቅድ ለሀገራቸው አንድነትና ለሕዝባዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰሩ ዘንድ፣ ይደራጁ ዘንድ እንሠራለን፣ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን። ወጣቶች ለዘመናት ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ቀዳሚ ፋና ወጊ ቢሆኑም ይህን ሁሉ መከራ ይዘው ዛሬም ሀገራቸውን፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን እንዴት እንደሚወዱ እየተመለከትን ነው። ሆኖም አድማጭ ይፈልጋሉ፣ አቅጣጫ የሚያሲዛቸውን ይመለከታሉ፣ እገዛ ያስፈልጋቸዋል። አንዴ መስመር ከያዘ ድብቅና እምቅ ችሎታቸውን ያወጡታልና ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል እንላለን።

ወደድንም ጠላን ሀገር ተረካቢ ትውልድ ከዛሬው ወጣቶች ነውና የሚፈልቀው ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ተማሪዎች፣ ታዳጊ ሕፃናት፣ “ወያላና ቦዘኔ” ተብለው እተገፉ ሥራአጥ ወገኖቻችን ላይ ትኩረት ያደረገ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ያደረገ ትውልድ አድን ተግባር ላይ እንሠራለን። ለዚህ ደግሞ እጅግ

ወደ ገፅ 24 ዞሯል »

## ትግል ወሬ... (ከገጽ 15 የዞረ)

በርካታ ቆራጥ ወጣቶች እንዳሉ ታዝበናል፣ ተመልክተናል። የሚያያቸው አጡ እንጂ።

ጠያቂ፦ አሁን ያለውን የለውጥ ሂደት ከክልል አደረጃጀት፣ ከቀጣዩ ምርጫ አንፃር እንዴት ትመለከቱታላችሁ?

አቶ ነሲቡ ስብሐት፦ የዛሬ ዓመት አካባቢ የጠቅላይ ሚንስትርነቱን የተረከቡት ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በዚህ ቆይታቸው የሠሩትና ያደረጉት እንደተጠበቀ ሀገራችንና ሕዝባችን ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ ነው ይበልጥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ።

ዛሬ በሀገራችን ጎልቶ የሚታየው የዘር ፖለቲካ ነው። ትግራይ የኢሕአዴግ መሥራችና ዋልታ በሆነው ህወሓት ተይዛ ትገኛለች፣ ኦሮሚያ በሚባለው አከላለል የጠቅላይ ሚንስትሩ ኢዴፓና ኦነግ እየተከታተሉት ይገኛሉ፣ በአማራ አካባቢ ከነግጭቱ በአማራነት የተደራጁ ኃይሎች ይታያሉ፣ በምሥራቁ ኢትዮጵያ የኦብነግ አብላጫውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፣ በደቡቡ የደቡብ ሕዝቦች የተለየ አካሄድ አለ፣ እንዲሁም የጋምቤላው፣ አፋሩ፣ ሌሎችም። ሀገራችን ከአንድነቷ ይልቅ እያንዳንዱን ክፍል ቆልፎ ለብቻው እንደሚተያይ፣ እንደሚጠባበቅ ቤተሰብ ሆናለች። ሁሉም ማለት ይቻላል የዘር አካሄዱን እያጠናከረው መጥቷል።

ከዚህ በተጨማሪ የኢሕአዴግ ሕገ መንግስት ያስቀመጠው የማንነት ጣጣ ብቅ እያለ በክልል ላይ ክልል እየተጠየቀ ነው። በአማራ የቅማንት፣ በደቡብ የሲዳማ፣ ሌላም ጉዳዮች ይታያሉ። ህወሓት በጉልበቱ የወሰደው የወልቃይት ጉዳይ ሕይወት እየቀጠፈ ነው። የጋምቤላ ኢትዮጵያውያኖች ዕምባ ዛሬም አላባራም። በደቡብ በርካታ ሕይወት ጠፍቷል መፈናቀሉም እንዲሁ። በምሥራቁ የኦሮሞ ተወላጆች እየተሰደዱና ሕይወት እየጠፋ ነው። ከሁሉም በላይ በአማራው ላይ በተለይ ጎንደር ሕዝብ ላይ ፍጅቱ ቀላል አይደለም።

ወደ አዲስ አበባም ስንመጣ ይህ ሕዝብን የሚያባላ ሕገ መንግሥት የሰነቀረውን አንቀጽ በመጠቀም አዲስ አበባን በኦሮሞ ክልል ለማድረግ የሚደረገው ፍጥጫ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በቅድሚያ የዘር አደረጃጀትና ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረግ የግዛት ክልል እስካላበቃ ድረስ ይህ ሁኔታ ወደ አደገኛ አካሄድ ላለመዝዙ ምንም ዋስትና የለንም።

ሕገ መንግስቱ በዘር መደራጀትንና መካለልን እስከፈቀደ፣ በአንድ ክልል ውስጥ ተበደልሁ ያለ ጎሳ ሌላ የማንነት ጥያቄ በመጠየቀ ለመገንጠል እስከፈቀደ ድረስ ችግሩ ያለው የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ላይ ለመሆኑ ደፍረን መናገር ይኖርብናል። ይህንን ሕገ መንግሥት ተገን በማድረግ ነው በዘር የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁኔታውን አጋግለው እዚህ ያደረሱት። ለዚህ ደግሞ በአለፈው የኢሕአዴግ ጉባኤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ኢትዮጵያ እንደሰበኩ የዘር ድርጅቶች የሚከስሙበትን አቅጣጫ ያሲዛሉ፣ ሕገ መንግሥቱ እንደገና የሚታይበትን ሁኔታ ያስቃኛሉ ተብሎ ሲጠበቅ ይባስኑ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን ወደ ፓርቲ አሳድገው ግቱበት፣ ሕገ መንግሥቱንም መመሪያችን አሉት። በመሆኑም የለውጥ ሂደቱ ጎልቶ የሚታየው ዘረኝነትን ይበልጥ ማጠናከሩ ላይ ነው።

ስለ ቀጣዩ ምርጫ ጉዳይ ሲታይ ከላይ እንደገለጽኩት እስቲ አሁን ያለውን ሁኔታ እንመልከተው። ዋና ዋና የተባሉት ክልሎች ኅብረ ብሔር ድርጅቶች በክልላቸው እንዳይንቀሳቀሱ ዘግተው ምን ሊከስት እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

አሁን በአለው ሁኔታ ለቀጣይ ምርጫ ከተደረሰ፤ በቀጣዩ ምርጫ በትግራይ ህወሓት ከአረና ትግራይ ተወዳድሮ ወይም ተስማምተው ትግራይን ይወስዳሉ። በኦሮሞ ጠቅላይ ሚንስትሩ የሚመሩት ኢዴፓ ከኦነግ ተወዳድሮ ወይም ተስማምተው ምናልባት አዲስ አበባንም ጠቅልለው ይወስዳሉ። በአማራው ብአዴን አሁን ከተፈጠሩት የአማራ ድርጅቶች ጋር ተወዳድሮ አማራ ክልልን ሊጠቀልል ይሞክራል ወይም አማራን ለማጥቃት የተዘጋጀው ዘመቻ ቀጥሎ በክልሉ አስከፊ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በሶማሌ ክልል ያለምንም ተቀናቃኝ ምሥራቁን የሀገራችንን ክፍል ኦብነግ ይወስደዋል። ሕገ መንግሥቱ የፈጠረው ችግር እንጂ በኢትዮጵያዊነታቸው ሁሌም የሚኮሩት የአፋር፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ ሕዝቦች ሁኔታም ተበታትኖ መቅረት ነው። እና በዚህ ሁኔታ ነው የሚቀጥለው ምርጫ የተዘጋጀው።

በእኛ በኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ አቋም መሠረት በሀገሪቷ የሥርዓት ለውጥ ያስፈልጋል ስንል ዘርን ተገን ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት ማብቃት አለበት ባይ ነን፣ ለዚህም የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት መቀየር ይኖርበታል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም በሚገባ ተወያይቶበትና መክሮበት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ለሕዝብ ክፍት የሆነ ውይይት መካሄድ ይኖርበታል። ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ የሽግግር መንግሥት አያስፈልግም እኔ አሻግራችኋለው ያሉት በዚህ መልክ ከሆነ እውነት ተሳስተዋል። ኢትዮጵያዊ እንዳሉት በቆራጥነት ቀጣዩን ምርጫ አራዝመው ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል አብቅቶ "ሁሉም ዘሮች ለኢትዮጵያ፣ የሁሉም ዘሮች ክልል ኢትዮጵያ" ብለው መነሳት ይኖርባቸዋል።

በ "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መሠረተ ሃሳብ የአከላለል አማራጮችን በልሳናችን "ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 2 ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም. "የዘር/ ቋንቋ ክልል ሲሉን አንድ ሀገር ስንል" በሚል በአቀረብነው መሠረት በተጨማሪ ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ለውይይት የቀረበ ሠነድ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የተላከ ሃሳብ የግዛት አከላለል አማራጮችን አቅርበናል።

በዚህ መሠረት 1. የቀድሞ ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር 2. የቀድሞ አውራጃን ያማከለ አስተዳደር 3. የመልክዓ ምድር ተፋሰስ ወንዞች አከላለል በሚል ያቀረብነው አማራጮችን የያዘ ሠነድ አሁንም ኢትዮጵያን ወደ አንድነት ለማምጣት በር ከፋች የመወያያ ሠነድ ነውና በመንግሥት ደረጃ ትኩረት እንዲሠጠው በድጋሚ እንጠይቃለን።

ያለበለዚያ ስለ ልማት ቢያወሩት አንድ ክፍልን አላስገባ ብሎ፣ እኔ ክፍል አትመጣም ተብሎ ልማት አይሠራም።

ጠያቂ፦ የኢሕአዴግ/ህወሀት 27 ዓመት አገዛዝ በምን መልኩ ትገመግሙታላችሁ?

አቶ ነሲቡ ስብሐት፦ በአለፈው ለ27 ዓመት ኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝቧ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ አስከፊ አደጋና ችግር ተዳርገዋል ሁኔታዎችም እጅጉን እየከፉ የመጡበት ወቅት ነው። ኢትዮጵያ በማንም ሀገር ላይ ነግሦ ከማያውቅ ቀጥቃጭ እጅ ወድቃለች።

- በፖለቲካው ረገድ ስናይ የህወሓት/ ኢሕአዴግ አገዛዝ ሲጀመር ሀገሪቷን በዘርና/ ቋንቋ ክልል ከመከፋፈሉም በላይ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን በማሽመድመድ ዘረኝነት ጎልቶ እንዲወጣ ጥረት አድርጓል።

- ለ27 ዓመታት በማጭበበር፣ በጉልበት፣ በንቀት ያለምንም ተቀናቃኝ ዴሞክራሲን ሽፋን አድርጎ የገዛ ብቸኛ አገዛዝ ነው። ለዚህም ምሳሌ የ1997 ዓ.ም. የተሸነፈበትን ምርጫ በጉልበቱ ወስዶታል፣ በቀጣይነት የመጡትን ምርጫዎች አንዴ 99.6 ቀጥሎ 100 በመቶ አሸነፍሁ እያለ ሀገርና ሕዝብን የናቀ አገዛዝ ነው።

- በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ የአንድ ነገድ የበላይነት የሰፈነበት እና የፖለቲካ ስርዓቱ ግፈኛና አሳታፊ ያልሆነ መሆኑን ተረድቶአል።

- በኢኮኖሚው መስክ በአገዛዝ ዘመናቸው የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት ሲዘርፉ፣ በገደብ-ጊዜ (Lease) ስም ለባዕዳን ባለሀብቶች ሲሸጡ ኖረዋል። ምስኪን ነዋሪውን ባልተጠና መንገድ ከኖረበት ቀዬ እያፈናቀሉ የላስቲክ ቤትና የጎዳና ተዳዳሪ በማድረግ እነሱ ቦታውን ለባለሀብቶች እየቸበቸቡ ጥሬ ገንዘብ ሲያካብቱ ኑረዋል። በማዳበሪያ ስም አርሶ አደሩን ከማስቀየት አልፈው የሀገራችንን ብርቅዬ ሰብሎች እያመከኑና በመጤ ዲቃላ ዘሮች እየበረዙ ይገኛሉ። በዚህና የሌሎች ጥርቅሞች ውጤት ሀገሪቷን ወደ ዕድገትና ስልጣኔ ጎዳና ከመውሰድ ይልቅ ዛሬ የተራበውን ሕዝብ፣ በቀን አንዴ ተመጋቢውን፣ ከየምግብ ቤቱና ሆቴሉ ትርፍራፊ ገኘውን ቤቱ ይቁጠረው። ኩሩ ወገናችን ዛሬ ከቆሻሻ ገንዳ የሚበላ ሲፈልጉ ማየት ምን ያህል የኢሕአዴግ አገዛዝ ሕዝባችንን አዘቅት ውስጥ እንደከተተ አመላካች ነው።

- በባህሉ ብንቃኝ የሀገራችን አኩሪ ባህልና ሰው አክባሪነት እንዲጠፋ፣ አኩሪ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ዕምነታችን እንዲበረዝ፣ ሕፃናት በየትምህርት ቤቱ ከሀገራቸው ታሪክ ይልቅ የባዕዳኑን አምላኪ እንዲሆኑ የሚደረገው ጥረት፣ ከትግራይ

ክልል ውጪ የሆኑ ወጣቶችን የተለያየ ሱስ ተጠቂዎች ይሆኑ ዘንድ የተሸረበው ተንኮል ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው ሀገራችን ጠንካራ ተኪ ትውልድ እንድታጣ በኢሕአዴግ/ ህወሓት በኩል የተደረገው ጥረት ቀላል አይደለም:: የሀገር ተተኪ ትውልዷ ከተኮላሸ ዕድገት ሳይሆን ውድቀት እንደምታስመዘግብ አያጠያይቅም::

በአጭሩ እነኚህን ሁኔታዎች ስንቃኝ ኢሕአዴግን ማዕከል ያደረገው ህወሓት ገና ሥልጣኑን እንደተቆናጠጠ ይዞ የተነሳው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማዳከም ዕቅዱ ነው ዛሬ ላይ ለውድቀት እያንደረደረው ያለው::

በጥቅሉ በወያኔ አገዛዝ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ መስኩ ኢትዮጵያ ተጎድታለች ተዳክማለች::

ህወሓት/ወያኔ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንዳትኖር ከሥልጣን ዘመኑ ጀምሮ ታሪኳን ሲያንቋሽሽ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን ሲያራክስ እንደነበር አይዘነጋም:: በሩቅ ጊዜ ትልማቸውም ኢትዮጵያን አንድነትና ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ለማጥፋት አነጣጥረው የመጡባቸው ሦስት ጉዳዮች አሉ:: እነሱም፡-

1. የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ማጥፋት:: ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ ቅርሶች መዝረፍ፣ ገዳማትን ማዳከም፣ ማውደም፣ ምእመናንን ማሰደድ

2. የአማራን ዘር ማጥፋት:: በረቀቀ የዘር ማጥፋት አማራውን መፍጀት፣ ማደህየት፣ ማደንቆር:: አማራው በሌሎች ጎሳዎች/ነገዶች እንዲጠላ መዝመት፣ የአማራ ሴቶች እንዳይወልዱ ማምከን

3. የዓፄ ምኒልክን ታሪክ መበረዝ:: ለኢትዮጵያ አንድነትና ለግዛት ሉዓላዊነት የጥቁር ሕዝብ ታሪክ የሠሩትን ምኒልክ በወራሪነት ታሪካቸውን መበረዝ፣ በጡት ቆራጭነት ሐውልት መሥራት

ይህ በ27 ዓመታት የኢሕአዴግ/ወያኔ አገዛዝ ተግባራዊ ሆኗል፣ እየሆነም ይገኛል:: በዚህ መልኩ ኢትዮጵያን በዘርና በቋንቋ ከፋፍለው በመንግሥት ስም የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት በመዝረፍና ያቃታቸውን በማውደም ሊገዙ ካልሆነም በጠነሰሱት የዘር ፖለቲካ ሀገሪቷን ሊበትኑ ለኢትዮጵያ መዳከም ከሚጥሩ ባዕዳን ጋር በዕቅድ የተጓዙ/የሚጓዙ መሆናቸው በሚገባ ሊጤን ይገባዋል::

ትዕግስትን የተላበሰው፣ መከራን ቻዩ ሕዝባችን መሠረታዊ ጉዳዮች ከተሟሉለት ብዙም አስቸጋሪ አይደለም:: የሀገራችን ሕዝብ ግና ያጣው መሠረታዊ የኑሮ ጉዳይ ነው:: መብላት አልቻለም፣ መጠለያ የለውም፣ ትውልዱ በተለያየ ሱስ እንዲጠቃ እየተደረገ ነው:: በሌላ በኩል ጥቂት ባለሀብቶች በተለይ ኢሕአዴግ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ ወዲህ ዝርፊያና ሙስናን ተገን አድርገው ዛሬ ጥጋብ ያሳወራቸው ባለሥልጣናትን በአንድ በኩል፤ በሌላ ጎኑ የአብዛኛው ሕዝብ መብላት ያቃተበት የኑሮ ደረጃ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት የሰማይና ምድር ያህል ነው::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን ሁኔታው ሻል ቢልም ሕዝባችን ያጣው መብቱን ነው:: እንደ ልቡ አይናገርም፣ አይጽፍም፣ አይሰበሰብም፣ አይዘዋወርም:: በተለያየ የወያኔ የስለላ መረብ ተቀፍድዶ ነበር ያለው:: ይህ እራሱ "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ" የሚለው የዛሬ 50 ዓመት የተነሳው ጥያቄ ዛሬም በአግባቡና ግልጽ በሆነ መንገድ ምላሽ ሳያገኝ ትግልን ጠያቂ ነው::

እነኚህን ሁላ ሁኔታዎች እልባት ሰጥቶ ኢትዮጵያ የልጆቿ እንድትሆን፣ የዜግነት መብት የተከበረባት ሀገር ከተመኘን፣ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት/ፓርቲ በነፃ ተንቀሳቅሶ ሕዝብ በመረጠው ሀገር ከተዳደረች፣ ለትውልድ ዘለቄታ ያለው ሕገ መንግሥት በአግባቡ ተረቆና በሕዝብ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን፣ ሕዝባችንን ከረሃብ፣ ከችግር፣ ከድንቁርና፣ ከበሽታ ወዘተ ለማላቀቅ ካሰብን በቅድሚያ የወያኔ አገዛዝ መወገድ አጠያያቂ አይደለም::

እነኚህ ሰዎች በ27 ዓመት አገዛዝ ዘመናቸው የሰሩት አንድ ነገር ቢኖር ወንጀል ነው:: ወንጀለኛ ደግሞ ሕግ ሊመለከተው ይገባል:: በሕዝብ ልጆች ደም፣ የሀገሪቷን ሀብት በመዝረፍ አላግባብ ብልጽግና ይጠየቃሉ:: ኢትዮጵያና ሕዝቧ የሚፈልጉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች እንፍታ ካልን ዘንዳ ለውጡ የጥገና ሳይሆን የሥርዓት መሆን ይኖርበታል::


SIRAK Advertising & Printing

ሲራክ ማስታወቂያና ህትመት

- ባነር - ስቲከር - ፍላየር -ቲሸርት ህትመት -የወረቀት ህትመት

09 33 93 57 75

አድራሻ፡ ካዛንቺስ ግሎሪ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ወይም

ከቶታል ወደ ዑራኤል ቤ/ያን በሚወስደው መንገድ ፖሊስ ጣቢያው ፊት ለፊት



ማህተም እንቀርፃለን

ፎቶና ቪድዮ ቀረፃ